9ኛ ዓመት ቁጥር 13
9th Year No. 13

ባህር ዳር ሚያዝያ 12 ቀን 1996 ዓ/ም
Bahir Dar, 20th April , 2004

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ
የአማራ ብሔራዊ ክልል ምክር ቤት

ዝክረ ህግ

ZIKRE HIG

Of the Council of the Amhara National Regional State
in the Federal Democratic Republic of Ethiopia

በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

Issued under the auspices of the Council of the Amhara National Regional State

✉ 1324
ያንዱ ዋጋ ብር 3.50
Unit price 3.50

ማውጫ	Content
አዋጅ ቁጥር 100/1996 ዓ.ም. በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የማዕድንና የገጠር ኢነርጂ ሃብት ልማት ማስፋፊያ ጽ/ቤት ማቋቋሚያ አዋጅ	Proclamation No.100/2004 The Amhara National Regional State Mines and Rural Energy Resource Development Expansion Office Establishment Proclamation

አዋጅ ቁጥር 100/1996 ዓ.ም.
በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የማዕድንና የገጠር ኢነርጂ ሃብት ልማት ማስፋፊያ ጽ/ቤትን ለማቋቋም የወጣ አዋጅ

የማዕድን ዘርፍ በአጠቃላይ ለኢኮኖሚው በተለይም ለኮንስትራክሽን ዘርፍ ዕድገት የሚያበረክተው አስተዋጽኦ ከፍተኛ ቢሆንም ተስማሚ በሆነና ትኩረት እንዲሰጠው በሚያስችል አደረጃጀት ካለመደገፉና ካለመጠናከሩ የተነሣ የዘርፉን አስተዋጽኦ በሚጠበቀው ደረጃ ለማሣደግ ይቻል ዘንድ ይህንኑ ገቢራዊ የሚያደርግ ብቁ አደረጃጀት እንዲኖረው አድርጐ ማቋቋም ተገቢ ሆኖ በመገኘቱ፣

የዘርፉን ልማት ይበልጥ ለማፋጠን እንዲረዳ የተሻለ ከሚቀርበው ከኢነርጂ ዘርፍ ጋር አደራጅቶ ከዘላቂ ውጤታማነት አንፃር በሙያ ግብዓትም ሆነ በማቴሪያል አቅርቦት የሚደጋገፉበትን ምቹ ሁኔታ መፍጠር በማስፈለጉ፣

Proclamation No.100/2004
A Proclamation Issued to Establish the Amhara National Regional State Mines and Rural Energy Resource Development Expansion Office

WHEREAS, though the contribution of the sector of mining is entirely high for the economy, especially for the growth of the construction sector, it is not supported and strengthened in a suitable organizational structure enabling to provide it with emphasis, and yet with a view to promoting the benefit of the sector to the extent expected, and for realization of same it is thus found appropriate to establish efficient organizational structure;

WHEREAS, with a view to further facilitating the development of the sector, it is necessary to create conducive condition in order to organize same with that of the energy sector, which has better proximity to it, and thereby make them support each other with respect to sustainable productiveness, expertise input as well as material provision;

በክልሉ ውስጥ ሕገ-ወጥ የማዕድናት ምርትና ንግድ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተስፋፋ ከመሄዱ የተነሣ ሁኔታውን ለመለወጥ ተገቢውን የቁጥጥር ሥርዓት መዘርጋትና የተፈጥሮ አካባቢ ሚዛኑን ሳይጐዳ ሃብቱ በቁጠባ ተይዞና ለምቶ የህዝብ ተጠቃሚነት የሚረጋገጥበትንና ለመጪው ትውልድ የሚተላለፍበትን ሁኔታ ማመቻቸት ጠቃሚ እንደሆነ ስለታመነበት፤

WHEREAS, owing to the fact that illegal minerals exploitation and trading is spreading from time to time, it is believed important to facilitate the condition by putting in place an appropriate controlling mechanism to change the situation in order for the resource to be economically kept and developed without causing damage to the natural environment and thereby to ensure the benefits to the public and transfer same to the coming generation;

በአሁኑ ወቅት በስራ ላይ ያለው የገጠር ኢነርጂ ሃብት ልማት ማስፋፊያ ጽ/ቤት በዋነኝነት ገጠር ተኮር ሆኖ የተደራጀ ቢሆንም በክልሉ ውስጥ ከተማ ነክ የኢነርጂ ጉዳዩችን በባለቤትነት ተረክቦ የሚሰራ ተቋም ካለመኖሩ የተነሣ የተጠቀሰውን ጽ/ቤት የኃላፊነት ወሰን ማስፋትና ለዚሁ ተጨማሪ ተግባር አቅም እንዲያገኝ አድርጐ እንደገና ማቋቋም አስፈላጊ በመሆኑ፤

WHEREAS, in spite of that the Rural Energy Resource Development Expansion Office which is currently in effect is mainly organized being rural-oriented, there is not an institution that carries out urban related energy issues in the Region, and it is, therefore, necessary to re-establish the Office and expand the scope of its responsibility by causing it having additional capacity thereto;

የአማራ ብሔራዊ ክልል ምክር ቤት በተሻሻለው የክልሉ ሕገ-መንግስት አንቀጽ 49 ንዑስ አንቀጽ 3/1/ ስር በተሰጠው ስልጣን መሠረት ይህንን አዋጅ አውጥቷል።

NOW, THEREFORE, the Council of the Amhara National Region in accordance with the power vested in it under Article 49 Sub-Article 3(1) of the Revised Constitution of the Region hereby issues this proclamation.

ክፍል አንድ

ጠቅላላ ድንጋጌዎች

PART ONE

GENERAL PROVISIONS

1. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ "በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የማዕድንና የገጠር ኢነርጂ ሃብት ልማት ማስፋፊያ ጽ/ቤት ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 100/1996 ዓ.ም." ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

1. Short Title

This Proclamation may be cited as "The Amhara National Regional State Minerals and Rural Energy Resource Development Expansion Office Establishment Proclamation No.100/2004."

2. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ፡-

1. "ማዕድን" ማለት ማናቸውም ዋጋ ያለው የምድር ክፍል ሆኖ ወይም በምድር ላይ ወይም ውስጥ በተፈጥሮ ተከማችቶ የሚገኝ ሃብት ሲሆን ጨውን፣ የማዕድን ውሃንና የጂኦተርማል ክምችቶችን ይጨምራል።

2. Definition

Unless the context otherwise requires, in this proclamation:

1. "Minerals" means any naturally occurring substance of economic value forming part of or found or within the earth's crust, including salt, mineral water and geothermal deposits.

2. "ኢነርጂ" ማለት በዋነኛነት ከባዮማስ እንዲሁም ከውሃ፣ ከፀሃይ፣ ከነፋስ፣ ታዳሽ ካልሆኑ ምንጮችና ከሌሎች የተለያዩ ቁሣቁሶች የሚገኝና ለህብረተሰቡ አገልግሎቶች የሚውል ሃይል ነው::

3. "ባህላዊ የማዕድን ማምረት ሥራ " ማለት ያለ ማሽነሪ ድጋፍ በባህላዊ መንገድ ልዩ ልዩ ማዕድኖች የሚመረቱበትን እንቅስቃሴ የሚገልጽ ነው::

4. "አነስተኛ ደረጃ የማዕድን ማምረት ስራ " ማለት የማዕድን ስራዎችን አስመልክቶ የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሚኒስትሮች ም/ቤት ባወጣው ደንብ ቁጥር 182/1986 ዓ.ም. /እንደተሻሻለ/ አንቀጽ 2 ንዑስ አንቀጽ 2 ሥር እንደተመለከተው ከማዕድን ስፍራ በአመት የሚመረተው ማዕድን አዘል አፈርና ድንጋይ በደንቡ ከተወሰነለት መጠን ሚያልፍ ማናቸውም የማዕድን አይነት የሚመረትበት እንቅስቃሴ ነው::

5. "ቢሮ " ማለት የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ገጠር ልማት ቢሮ ነው::

ክፍል ሁለት

ስለማዕድንና ገጠር ኢነርጂ ሃብት ልማት ማስፋፊያ ጽ/ቤት መቋቋም ፣ተጠሪነት፣ አላማ፣ አወቃቀርና ስልጣን

3. ስለመቋቋምና ተጠሪነት

1. የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ማዕድንና ገጠር ኢነርጂ ሃብት ልማት ማስፋፊያ ጽ/ቤት /ከዚህ በኋላ "ጽ/ቤቱ " እየተባለ የሚጠራ/ ራሱን የቻለና ህጋዊ ሰውነት ያለው የክልሉ መንግስት አስፈፃሚ መስሪያ ቤት ሆኖ በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል::

2. የጽ/ቤቱ ተጠሪነት ለቢሮው ይሆናል::

2. " Energy" means the energy that is mainly obtained from biomass as well as water, the sun, wind, non-renewable sources and from other various materials and used for public services.

3. " Artisanal mining" means to describe an activity by which various minerals are produced traditionally without help of a machine.

4. " Small Scale Mining Operations " means any mining operation which the annual run off mine ore does not exceed the limit as indicated under sub-Article 2 of Article 2 of Regulation No. 182/1994 (as amended) issued by the Council of Ministers of the Federal Democratic Republic of Ethiopia concerning mining operations.

5. " Bureau" means the Amhara National Regional State Rural Development Bureau.

PART TWO

Establishment, Accountability, Objective, Organizational Structure and Power of mines and Rural Energy Resource Development Expansion Office

3. Establishment and Accountability

1. The Amhara National Regional State Mines and Rural Energy Resource Development Expansion Office /herein after referred to as " The Office"/ is hereby established as an autonomous Governmental executive Office as per this proclamation.

2. The Office shall be accountable to the Bureau.

4. ዓላማ

ጽ/ቤቱ በዚህ አዋጅ መሠረት የሚከተሉት አላማዎች ይኖሩታል፦

1. በክልሉ ውስጥ የሚገኙት የማዕድንና ኢነርጂ ሃብቶች ለምተው ለኢኮኖሚው የበኩላቸውን አስተዋጽኦ የሚያደርጉበትንና ከድህነት ለመውጣት የሚደረገውን ጥረት ማገዝ።

2. የገጠሩ ነዋሪ ህዝብ ሁለንተናዊ የኢነርጂ ፍላጐት በላቀ ደረጃ ይሟላ ዘንድ አማራጭና ተስማሚ የኢነርጂ ምንጮችና ቴክኖሎጂዎች የሚለሙበትና የሚስፋፉበትን ምቹ ሁኔታ መፍጠር።

3. የማዕድንና የኢነርጂ ሃብት ያለአግባብ እንዳይባክንና በልማቱ ወቅት አካባቢው እንዳይበከልና እንዳይጐዳ አስፈላጊውን ቁጥጥር ማድረግ ፣መጠበቅና ለመጪው ትውልድ ማስተላለፍ።

5. መደበኛ አድራሻ

የጽ/ቤቱ መደበኛ አድራሻ በባህርዳር ከተማ ሲሆን እንደአስፈላጊነቱ በሌሎች ስፍራዎች የአካባቢ ቅርንጫፍና ማስተባበሪያ ጽ/ቤቶችን ሊያቋቁም ይችላል።

6. የጽ/ቤቱ ስልጣንና ተግባር

ጽ/ቤቱ በዚህ አዋጅ መሠረት የሚከተሉት ስልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፦

1. በክልሉ ውስጥ የማዕድንና ኢነርጂ ልማት እንዲስፋፋ ጥናቶችን ያካሂዳል፣ እንዲጠኑ ያደርጋል፣

2. የግል ባለሃብቶች በማዕድንና ኢነርጂ ልማት ስራዎች በስፋት እንዲሳተፉ ይቀሰቅሳል፣ የተለያዩ የፕሮሞሽን ስራዎችን በማከናወን ያበረታታል፣

4. Objective

The Office shall, pursuant to this proclamation, have the following objectives:

1. Support the effort made to get out of poverty through the development of mineral and energy resources found in the Region and making same contribute their benefit to the economy.

2. Create conducive condition whereby alternative and suitable energy resources and technologies develop and expand in order to meet the over-all energy demand of the rural dwelling people to the best extent.

3. Make the necessary control and protection that mineral and energy recourses not to be wasted and the environment remains unpolluted and undamaged in time of exploitation, and thereby transfer same to the coming generation.

5. Main Address

The regular address of the Office shall be in Bahir Dar, and may establish branch and co- coordinating Offices in other places as deemed necessary.

6. Powers and Duties of the Office

The Office shall, pursuant to this proclamation, have the following powers and duties:

1. Conduct studies as well as cause same to be undertaken so as to expand mineral and energy development in the Region;

2. Initiate and encourage through undertaking various promotion activities that private investors take part broadly in mineral and energy development activities;

3. ዘርፉ ለላቀ ኢኮኖሚያዊ ዕድገት ውጤታማ አስተዋጽኦ እንዲያበረክት አደረጃጀቱን በማሻሻልና አቅሙን በመገንባት ረገድ ተገቢውን ጥረት ያደርጋል፤

4. ማዕድንና ኢነርጂን አስመልክቶ በሀገሪቱ የወጡ ህጐች በክልሉ ውስጥ በስራ ላይ መዋላቸውን ያረጋግጣል፣ ይቆጣጠራል፤

5. በክልሉ ውስጥ የኤሌክትሪክ ኃይል አቅርቦትን ለማጻረስ የዲዝል፣ የፀሃይ ሃይልና አነስተኛ የውሃ ሃይል ማመንጫ ጣቢያዎች ስለሚቋቋሙበት ሁኔታ ያጠናል፤

6. የግል ባለሃብቶች ጥያቄ ሲያቀርቡለት አነስተኛ የኤሌክትሪክ ኃይል ለማምረት በሚያስፈልገው ሜጋ ዋት መጠን አግባብ ካላቸው የፌዴራሉ መንግስት አካላት ጋር በመመካከርና እንደአስፈላጊነቱም የሥልጣን ውክልና ሲሰጠው ኤሌክትሪክ የማመንጨትና የማሠራጨት ሥራ ፈቃድ ይሠጣል፣ ይቆጣጠራል፤

7. ክልሉ ከዋናው የአገሪቱ የኤሌክትሪክ ግሪድ የሀይል ተጠቃሚ በሚሆንባቸው ጉዳዩች ላይ ይተባበራል፣ መረጃ ይሰጣል፤

8. ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር በባህላዊ መንገድና በአነስተኛ ደረጃ የሚካሄድን የማዕድን ሃብት ፍለጋ፣ ምርመራ፣ ግኝትና ምርት ፈቃድ ይሰጣል፣ ያድሣል፣ ይሠርዛል፤

9. ባህላዊና አነስተኛ የማዕድን ማምረት ስራዎችን ይደግፋል፣ የማዕድን ህብረት ስራ ማህበራት በክልሉ ውስጥ እንዲስፋፉ ያበረታታል፤

10. ሕገ-ወጥ በሆነ መንገድ የሚከናወን ማናቸውም የማዕድን ሃብት ምርትና ንግድ እንቅስቃሴ እንዲገታ አስፈላጊውን የቁጥጥር ስርዓት ይዘረጋል፣ ይቆጣጠራል፣ በሕገ-ወጥ መንገድ ተይዘው የተገኙ ማዕድናት በአግባቡ ተጠብቀው ሕጋዊ ውሣኔ እንዲያገኙ ያደርጋል፤

3. Put an appropriate effort with regard to improving the organization of the sector and building its capacity so that it makes effective contribution for higher economic growth;

4. Ensure and supervise that laws promulgated in the country concerning minerals and energy are implemented in the Region;

5. Undertake studies concerning the establishment of diesel, sunlight power and small-scale hydropower stations with a view to the supplying of electrical energy in the Region;

6. Permit and supervise, in consultation with appropriate organs of the Federal Government and delegation of power conferred upon it as deemed necessary, where private investors submit a request for generating and supplying of electric power with the amount of mega watt required to produce small scale electric power;

7. Co-operate and provide information on issues that the Region becomes beneficiary from the main electric power grid of the country;

8. Issue, renew and cancel, in co-operation with concerned bodies, license of mineral resources' exploration, investigation, finding and exploitation being undertaken traditionally and in small scale;

9. Support traditional and small scale mineral exploitation works, and encourage the expansion of co-operative associations of mineral works in the Region;

10. Put in place the necessary controlling system and thereby supervise to restrain any illegal exploitation and trading activity of mineral resources; cause minerals found illegally seized properly kept and get a verdict thereof;

11. በአማራጭ የገጠር ኢነርጂ አቅርቦት ረገድ የተለያዩ የኢነርጂ አማራጭ ቴክኖሎጂዎች በሠርቶ ማሣያ ሙከራ እንዲስፋፉ ያደርጋል፣ የማበረታቻ ስራዎችን በስፋት ያከናውናል፣

12. የገጠር ኢነርጂን ለማስፋፋት ይቻል ዘንድ ተጠቃሚዎች እና የቴክኖሎጂ አምራቾች ተደራጅተው የብድር አገልግሎት የሚያገኙበትን ሁኔታ ያመቻቻል፣

13. አገር በቀል የኢነርጂ ቴክኖሎጂዎችን ያበለጽጋል፣ ከውጭ ሃገር የሚገኙትን የኢነርጂ ቴክኖሎጂዎች ከክልሉ ፍላጐት ጋር በማጣጣም ያሳምጻል፣

14. የአካባቢ ጥበቃን ከግምት ውስጥ የሚያስገቡ ተመጣጣኝ ዋጋና ብቃት ያላቸውን የኢነርጂ ምንጮችና ቴክኖሎጂዎችን ልማት፣ ሥርጭት፣ አጠቃቀምና ቁጠባ ያጣራል፣ እንደሁኔታው በግል ባለሃብቶች፣ በመንግስትና በሌሎች ዘርፎች በኩል ለህብረተሰቡ ያስተዋውቃል፣

15. በክልሉ ውስጥ የማገዶ ተክል በስፋት እንዲለማና የማገዶ አቅርቦት የህብረተሰቡን ፍጆታ የበለጠ እንዲሆን አግባብ ካላቸው አካላት ጋር ይሰራል፣

16. የተለያዩ የማዕድንና ኢነርጂ ምንጮችን መጠቀም የሚያስከትለውን ማህበራዊ ተፅእኖ ይገመግማል፣

17. በማዕድን ሃብት ልማት ሂደት የሚገኝ የሮያሊቲና ሌሎች ተዛማጅ አገልግሎቶች ክፍያዎችን ይሰበስባል፣

18. ማዕድንና ኢነርጂን የሚመለከቱ መረጃዎችን ይሰበስባል፣ ይተነትናል፣ ያደራጃል፣

19. አላማውን ከሚደግፉ ከአገር በቀል፣ ከውጭ ሃገርና ከዓለማቀፍ ድርጅቶች ጋር ይተባበራል፣

20. የንብረት ባለቤት ይሆናል፣ ውል ይዋዋላል፣ በስሙ ይከሣል፣ ይከሰሣል፣

11. Cause the expansion of various alternative energy technologies in demonstration centers with regard to the supply of alternative rural energy, and broadly carry out activities of encouragement thereof;

12. Facilitate the condition whereby users and technology producers organize themselves and get credit service with a view to expanding rural energy;

13. Enrich indigenous energy technologies, and adopt energy technologies from abroad to the need of the Region;

14. Verify the development, distribution, consumption and frugality of energy sources and technologies with equitable price and efficiency that take into account environmental conservation; and thereby introduce same to the community through private investors, government and other sectors as the circumstance being so;

15. Work with relevant bodies to widely cultivate firewood and the supply of same exceeding the consumption of the community in the Region;

16. Evaluate the social influence brought by exploiting various mineral and energy sources;

17. Collect charges of royalty and other related services gained in the process of exploiting mineral resources;

18. Collect, analyze and organize data relating to minerals and energy;

19. Co-operate with indigenous, overseas and international organizations that support its objective;

20. Own property, inter into contracts, sue and be sued;

21. ዓላማውን ከግብ ለማድረስ የሚያስፈልጉ ሌሎች ሕጋዊ ተግባራትን ያከናውናል።

7. ድርጅታዊ አቋም

ጽ/ቤቱ፦

1. በቢሮው አቅራቢነት በርዕሰ መስተዳድሩ የሚሾም የጽ/ቤት ኃላፊ፣

2. አስፈላጊ የስራ ክፍሎችና ሰራተኞች ይኖሩታል።

8. የጽ/ቤቱ ኃላፊ ስልጣንና ተግባር

1. የጽ/ቤቱ ኃላፊ የጽ/ቤቱ ዋና ስራ አስፈፃሚ ሆኖ ከቢሮው በሚሰጠው አጠቃላይ መመሪያ መሠረት የጽ/ቤቱን ስራዎች በበላይነት ይመራል፣ ያስተባብራል።

2. ከዚህ በላይ በንዑስ አንቀጽ 1 የተጠቀሰው አጠቃላይ አንጋገር እንደተጠበቀ ሆኖ የጽ/ቤቱ ኃላፊ፦

ሀ. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 6 ስር የተመለከቱትን የጽ/ቤቱን ስልጣንና ተግባራት በስራ ላይ ያውላል፣

ለ. በክልሉ ሲቪል ሰርቪስ ህግ መሠረት የጽ/ቤቱን የበታች ሥራ ኃላፊዎችና ሌሎች ሰራተኞች ይቀጥራል፣ ያስተዳድራል፣

ሐ. የጽ/ቤቱን የስራ ፕሮግራምና የማስፈፀሚያ በጀት ረቂቅ አዘጋጅቶ በቢሮው አማካኝነት ለክልሉ መንግስት ያቀርባል፣ ሲፈቀድም በተግባር ላይ ያውላል፣

መ. ከሦተኛ ወገኖች ጋር በሚደረጉ ግንኙነቶች ሁሉ ጽ/ቤቱን ይወክላል።

21. Carry out other legal functions necessary to achieve its objectives.

7. Organizational Structure

The office shall have:

1. Office Head appointed by the Head of the Government upon recommendation by the Bureau;

2. Necessary departments and staff.

8. Powers and Duties of the Head of the Office

1. The Head of the Office being the Chief Executive of the Office shall direct and co-ordinate over the functions of the Office in accordance with the general directives as given to him by the Bureau.

2. Without prejudice to the generality of the stipulation of sub-Article 1 of this Article, the Head of the Office shall:

A. Implement the powers and duties of the Office stipulated under Article 6 of this proclamation;

B. Employ and manage lower officials and other staff members in accordance with the Regional Civil Service Law;

C. Prepare and submit the work program and draft budget execution of the Office to the Regional Government through the Bureau, and execute same upon approval;

D. Represent the Office in all its relations with third parties.

3. የጽ/ቤቱ ኃላፊ ለጽ/ቤቱ የስራ ቅልጥፍና በሚያስፈልገው መጠን ስልጣንና ተግባሩን በከፊል ለጽ/ቤቱ የስራ ኃላፊዎችና ለሌሎች ሰራተኞች በውክልና ሊያስተላልፍ ይችላል።

ክፍል ሦስት

ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

9. የበጀት ምንጭ

የጽ/ቤቱ በጀት ከሚከተሉት ምንጮች የሚገኝ ይሆናል፦

1. ከመንግስት የሚመደብ ዓመታዊ በጀት፣
2. ከሌሎች ምንጮች የሚገኝ የአይነትም ሆነ የጥሬ ገንዘብ ድጋፍ።

10. የሂሣብና የንብረት መዛግብት

1. ጽ/ቤቱ የተሟሉና ትክክለኛ የሆኑ የሂሣብና የንብረት መዛግብትን ይይዛል።
2. የጽ/ቤቱ የሂሣብ መዛግብትና ሌሎች ገንዘብም ሆነ ንብረት ነክ ሰነዶች በክልሉ ዋና አዲተር መሥሪያ ቤት ወይም እርሱ በሚሰይመው ሌላ አዲተር ይመረመራሉ።

11. የተሻሩና ተፈፃሚነት የማይኖራቸው ሕጐች

1. የሚከተሉት በዚህ አዋጅ ተሽረዋል፦
   ሀ. የገጠር ኢነርጅ ሃብት ልማት ማስፋፊያ ጽ/ቤት ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 71/1994፤
   ለ. የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት አስፈፃሚ አካላት ማቋቋሚያና ስልጣንና ተግባራት መወሰኛ አዋጅ ቁጥር 4/1988 ዓ.ም. /እንደተሻሻለ/ አንቀጽ 10 ንዑስ አንቀጽ 8፣ 10፣ 11፣ 12፣ 13 እና 14 ድንጋጌዎች፤

3. The Head of the Office may delegate part of his powers and duties to the Heads and other staff members of the Office in as much as such delegation is required for the expedition of the task of the Office thereto.

PART THREE

Miscellaneous Provisions

9. Budget Source

The Budget of the Office shall be drawn from the following sources:

1. Annual budget allocated by the Government;
2. Assistances from other sources in cash or in kind.

10. Books of Account and Property

1. The Office shall keep complete and accurate books of account and property.
2. The books of account and other financial as well as property related documents of the Office shall be audited by the Office of the Auditor-General of the Region or by another auditor designated by him.

11. Repealed and Inapplicable laws

1. The following shall be repealed by this proclamation:
   a. Rural Energy Resource Development Expansion Office Establishment Proclamation No. 71/2002;
   b. Provisions of sub-Articles 8,10, 11, 12, 13 and 14 of Article 10 of the Establishment and Determination of Powers and Duties of the Amhara National Regional State Executive Organs Proclamation (as amended) No. 4/1995;

ሐ. በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት አስፈፃሚ አካላት እንደገና ማደራጃና ስልጣንና ተግባራት መወሰኛ አዋጅ ቁጥር 60/1994 ዓ.ም. ማዕድንን የሚመለከቱት የአንቀጽ 15 ድንጋጌዎች።

2. ከዚህ አዋጅ ጋር የሚቃረን ማናቸውም ህግ፣ ደንብ፣ መመሪያ ወይም የተለመደ አሠራር በዚህ አዋጅ ውስጥ በተመለከቱት ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት አይኖረውም።

12. መብትና ግዴታን ስለማስተላለፍ

በአዋጅ ቁጥር 60/1994 አንቀጽ 15 ስር ለተቋቋመው የውሃና ማዕድን ሃብት ልማት ቢሮ የተሰጡት ማዕድን ነክ ኃላፊነቶችና በአዋጅ ቁጥር 71/1994 ለተቋቋመው የገጠር ኢነርጅ ሃብት ልማት ማስፋፊያ ጽ/ቤት የተሰጡት መብቶችና ግዴታዎች በዚህ አዋጅ ወደ ተቋቋመው ጽ/ቤት ተላልፈዋል።

13. ደንብና መመሪያ የማውጣት ስልጣን

1. የአማራ ብሔራዊ ክልል መስተዳድር ምክር ቤት ይህንን አዋጅ ለማስፈፀም የሚያስፈልጉትን ደንቦች ሊያወጣ ይችላል።

2. ቢሮው ይህንን አዋጅና በዚህ አዋጅ መሠረት የሚወጡትን ደንቦች ለማስፈፀም የሚያስፈልጉትን መመሪያዎች ሊያወጣ ይችላል።

14. አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ በክልሉ መንግስት ዝክረ-ሕግ ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

ባህርዳር
ሚያዝያ 12 ቀን 1996 ዓ.ም.

ዮሴፍ ረታ
የአማራ ብሔራዊ ክልል
ፕሬዚዳንት

C. Mining related provisions of Article 15 of the Reorganization and Determination of Powers and Duties of the Amhara National Regional State Executive Organs Proclamation No. 60/2001.

2. Any law, regulation, directive or customary practices in consistent with this proclamation shall not be applicable on matters provided in this proclamation.

12. Transfer of Rights and Duties

Mining related responsibilities entrusted to Water and Mining Resource Development Bureau established under Article 15 of proclamation No. 60/2001 and the rights and duties entrusted to Rural Energy Resource Development Expansion Office established by Proclamation No. 71/2002 are hereby transferred to the Office established as per this proclamation.

13. Power to Issue Regulation and Directive

1. The Council of the Amhara National Regional Government may issue regulations necessary for the implementation of this proclamation.

2. The Bureau may issue directives necessary for the implementation of this proclamation and regulations to be issued in accordance with this proclamation.

14. Effective Date

This Proclamation shall come into force commencing the day of its publication in the *Zikre Hig Gazetta* of the Regional State.

Done at Bahir Dar,
This 20th Day of April, 2004

Yosef Retta
President of the Amhara National Region